# ለኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪ ክፍያ ኢኩዊቲ ፈንድ
# የትክክል ማራዘሚያ ጥያቄ ሂደት

በኤርሊቻይልድ ሁድ አስተማሪ ክፍያ ኢኩዊቲ ፈንድ ውስጥ ተሳትፎ የሚያደርጉ የልጆች እንክብካቤ ሰጪዎች ከፕሮግራሙ የቁጥጥር እና መገዛት ፕሮግራም መስፈርቶች ጋር አንድ ላይ መሄድ አለባቸው። የክትትል ፖሊሲው እዚህ ይገኛል። ክትትሉን ማጠናቀቂያ መመሪያ እዚህ ይገኛል። በልጆች ድጎማ ፕሮግራም ውስጥ ተሳትፎ ለሚያደርጉ አገልግሎት ሰጪዎች የቁጥጥር ሂደቱ በጥቂቱ የሚለይ ሲሆን ምክንያቱ ደግሞ እነዚህ አገልግሎት ሰጪዎች ቁጥጥርን የሚጨርሱት የድጎማ ፕሮግራም ቁጥጥር በሚደረግባቸው በዚያው ሰአት መሆኑ ነው።

አቅራቢዎች የክትትል ሂደቱን ለማጠናቀቅ የ 30 ቀን ማሳወቂያ ይሰጣቸዋል። የግዛቱ የትምህርት ተቆጣጣሪ ጽ/ቤት (OSSE) አንዳንድ የህፃናት እንክብካቤ አቅራቢዎች የቁጥጥር ሂደቱን ለማጠናቀቅ ተጨማሪ መረጃ መሰብሰቢያ ጊዜ ሊያስፈልጋቸው እንደሚችል ይረዳል። አገልግሎት ሰጪዎች በOSSE የታዘዘውን የገደብ ጊዜ እንዳያሟሉ የሚከላከሉ ተግዳሮቶችን ካጋጠማቸው ሂደቱን ለማጠናቀቅ ተጨማሪ ጊዜ ለማግኘነት ሊጠይቁ ይችላሉ። ማራዘሚያውን ለማግኘት አንድ አመልካች ጥያቄውን ለOSSE የክክትል ማብቂያ ቀን ማሳወቂያው በረደረሳቸው በሁለት ሳምንታት ውስጥ ሊያቀርቡ ይገባል።

## የሂደት እይታ

*የክትትል ማሳወቂያ*

ክትትል ሲጀመር OSSE ለልጆች እንክብካቤ አቅራቢዎችን በኢሜል ያሳውቃል። አገልግሎት ሰጪዎች ኢሜይል ከተላከላቸው ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ የተጠየቁትን ሰነዶች ለማቅረብ ጊዜ አላቸው።

*የማራዘሚያ ብቁነት*

ተደራራቢ የሆነ ግምገማ፣ አስተዳደራዊ ጫና ወይም የሰራተኛ እጥረት ያለባቸው የልጆች እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪዎች ማራዘሚያ ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ማራዘሚያውን ለማግኘት አንድ አገልግሎት አቅራቢ የክትትል ማብቂያ ቀን ማሳወቂያው በደረሰው በሁለት ሳምንታት ውስጥ ጥያቄ ለOSSE ማቅረብ አለበት።

*የማራዘሚያ ጥያቄ ማስገባት*

የክትትል የጊዜ ገደብ ማራዘሚያ ለመጠየቅ የልጆች እንክብካቤ አቅራቢ ለ OSSE.ECEPayEquity@dc.gov በኢሜል ጥያቄ ማስገባት አለበት። ጥያቄው የሚከተለውን መረጃ ማካተት አለበት፡-

- የአገልግሎት ሰጪ ስም
- የፋሲሊቲ ስም እና ፈቃድ ቁጥር (በጥያቄው ውስጥ ለተካተቱ ሁሉም ተቋማት)
- የእውቂያ ሰው (ስም፣ ኢሜይል፣ ስልክ)
- የማራዘሚያ ጥያቄ ምክንያት
- የታቀደው አዲስ የማስረከብ ቀን (ከመጀመሪያው ቀናት በኋላ ከ 60 ቀናት አይብለጥ)

*ግምገማ እና ማፅደቅ*

OSSE እያንዳንዱን ጥያቄ በጉዳዩ ላይ በመመርኮዝ ይገመግማል። የልጆች እንክብካቤ አቅራቢው የማራዘሚያ ጥያቄያቸውን ባቀረቡ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ምላሽ ይሰጣቸዋል። ጥያቄያቸው ተቀባይነት ካገኘ ወይም ውድቅ ከተደረገ OSSE ለአቅራቢው በኢሜይል ያሳውቃል። ጥያቄው ተቀባይነት ካገኘ OSSE የክትትል ሂደቱን ለማጠናቀቅ የአቅራቢውን አዲስ ቀነ ገደብ ያሳውቃል። በ OSSE የተሰጡት ውሳኔዎች የመጨረሻ ናቸው።

*የተገዢነት ክትትል*

ክትትል ለማጠናቀቅ ማራዘሚያ ያገኙ የልጆች እንክብካቤ አቅራቢዎች በOSSE የተሰጣቸውን አዲሱን ቀነገደብ ማክበር አለባቸው አለዚያ ቀነ ገደቡን እንዳላከበሩ ይቆጠርባቸዋል። ማራዘሚያ ያገኘ የልጆች እንክብካቤ አቅራቢ በOSSE የተሰጠውን አዲሱን የጊዜ ገደብ ካላሟላ ያ የልጆች እንክብካቤ አቅራቢ ተገዢ ያለመሆን እውቅና የሚሰጠው ይሆናል። የልጆች እንክብካቤ አቅራቢዎች ለአንድ የክትትል ጊዜ በርካታ ማራዘሚያዎችን መጠየቅ አይችሉም።

## የልጆች እንክብካቤ አቅራቢዎች ለፈንድ ክትትል ማራዘሚያ መጠየቅ የሚችሉበት ሂደት

1. **OSSE የአቅራቢ ክትትል እንደጀመረ ያሳውቃል**
   - OSSE የክትትል ሂደቱን በዝርዝር የሚያሳይ እና ሂደቱን ለማጠናቀቅ የተሰጠው ቀነ ገደብ መቼ እንደሆነ ቀደም ብሎ ለአቅራቢው ኢሜይል ይልካል።
2. **አቅራቢው በኢሜል ወደ OSSE የማራዘሚያ ጥያቄ ያቀርባል**
   - አቅራቢው የክትትል ጊዜ ማብቃቱን ከOSSE ማሳወቂያውን ከተቀበለ በኋላ ባሉት ሁለት ሳምንታት ውስጥ ወደ OSSE.ECEPayEquity@dc.gov ኢሜል ይልካል። ኢሜይሉ የአቅራቢውን ስም፣ የፋሲሊቲ ስም (ዎች) እና የፈቃድ ቁጥር (ዎች) (በጥያቄው ውስጥ ለተካተቱ ሁሉም ተቋማት)፣ የእውቂያ ሰው፣ የማራዘሚያ ጥያቄ ምክንያት እና የታቀደውን አዲስ የማቅረብ ቀን ማካተት አለበት።
3. **OSSE ጥያቄውን ይገመግማል እና ለአቅራቢው ውሳኔውን ያሳውቃል**
   - OSSE ጥያቄውን በተቀበለ አምስት የሥራ ቀን ውስጥ ገምግሞ እና ጥያቄው ተቀባይነት ካገኘ ወይም ውድቅ ከሆነ ለአቅራቢው በኢሜል ያሳውቃል።

## ጥያቄዎች

ማራዘሚያ በመጠየቅ ሂደት ላይ ጥያቄ ካለዎት ለ OSSE.ECEPayEquity@dc.gov ኢሜይል ይላኩ።